ENPCP

የኢትዮጵያ አበይት ጉዳዮች መወያያ ሂደት

Ethiopian National Priorities Consultative Process

P.O.Box 171, East Lansing, Michigan 48823, E-mail: secretariat@enpcp.org

ጋዜጣዊ መግለጫ --- ጃንዋሪ 20/2012

# ለኢትዮጵያዊነት

የኢትዮጵያ አበይት ጉዳዮች መወያያ ሂደት ለኢትዮጵያዊነት የተባለውን አዲስ የጽሁፍ ልሳን ለመጀመር መወሰኑን በደስታ ይግልጻል፤የመመረቂያው ቁጥር በቅርብ ቀናት ይታተማል፤

አሁን ላለንበት ወቅት ለኢትዮጵያዊነት በይዘቱ ለየት የሚያደርገው፤ ትኩረቱ በሲቪክ ማኅበራት ላይ ስለሆነ  የኢትዮጵያውያን የሲቪክ ማህበራትን ተቋም በሚመለከቱ አርእስቶች ላይ የሚገለጹትን ዜናዎች፤ገምቢ አስተያየቶች፤ ጠለቅ ያሉ ትንታኔዎችን እና  የመሳሰሉትን ለማስተናገድ የመወያያ  ሂደቱ ኃላፊነቱን ተቀብሏል።

የኢትዮጵያዊነትን ራዕይ ተቀብለው የሚራመዱ የኢትዮጵያውያን የሲቪክ ማህበራት በይበልጥ እንዲዳብሩ ለማድረግ የመወያያ ሂደቱ በድህረ ገጹና በ-ለኢትዮጵያዊነት ልሳኑ በመጠቀም ማናቸውንም አገልግሎት ስለሚፈጽምላቸው ማህበራቱ በሚከተሉትን ዓቢይ መሥፈርቶች ተመርኩዘው ሲራመዱ የኢትዮጵያዊነት አቋማቸውን በሚገባ እንደሚያበለጽግላቸው  የመወያያ ሂደቱ ባለ ሙሉ ተስፋ ነው። የሚከበሩት መሰፈርቶቹም ከዚህ በታች ተጽፈዋል ፦

- የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት
- የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት
- በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁት የግልና የሲቪል
- የፖሌቲካ ነፃነት መብቶች
- ለሁሉም እኩል የሆነ የአስተዳድር ሥራዓት
- በአንድነት የታቀፈ የብሄረሰቦች ባህል
- የንብረት ባልቤትነትና የኢኮኖሚ ነፃነት
- የሲቪክ ማህበራትን የሚያዳብር  ትብብር

በጠቅላላውም የኢትዮጵያን ሲቪክ ማህበራት ለማጠናከር፤ ገምቢ ሀሳብ እና ጽሁፍ የሚለግሱትን፣አስተማሪዎች፤ምሁራኖች እና የሌሎችንም ግለሰቦች ጠቃሚ ተምክሮዎችን በጥሞና እንቀበላለን።

በድህረ ገጻችን ወይም በ-ለኢትዮጵያዊነት አምዶች እንዲቀርቡ ጽሁፎች ለማበርከት ለሚሹ ሁሉ የሚከተሉት መመሪያዎች እንዲከበሩ የሂደቱ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል በአክብሮት ያሳስብል።

- በተጠቀሱት በሁለቱ ሚድያ ላይ ለሚቀርቡ ገንዝብ ውይም ሽልማት አይሰጥም
- የጽሁፉ አቅራቢ ሙሉ ስም እና አድራሻ መገለጽ ይኖርበታል
- ጽሁፎች በማይክሮሶፍት ፎርማት እንዲነደፉ ያስፈልጋል
- ሰዕሎች ተለይተው በጄፒኢጂ ፎርማት ብቻ መቅረብ ይኖርባቸዋል
- የሰዕሎች ዝርዝር አማካኞች መገለጽ ይኖርባቸዋል
- ተገቢ ያልሆኑ ድርሰቶች አይታተሙም
- የሚቀርቡት ጽሁፎች ካስፈለገ የሰዋሰውና የሆሄያት እርማት ይደረግባቸዋል
- እንደአስፈላጊነቱ የሚቀርቡትን ጽሁፎች ላለማተም የሂደቱ ህጋዊ መብት የተጠበቀ ነው
- የፎንትና የፎርማቲንግ ስልቶች በዋና አዘጋጁ ይስተካከላሉ

እባክዎ ለህትመት የሚቀርቡትን ጽሁፎች በቅድምያ ለሂደቱ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ለሆኑት ለወይዘሮ ለምለም ጸጋው ይላኩ።